# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

4

★ ጭቁን ሴቶችና ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት

★ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር

★ የቦልሼቪክ ፓርቲ አጭር ታሪክ

★ ጩኸቴን ቀሙኝ ፡

★ ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ

ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

ር እ ሰ አ ን ቀ ጽ

# ለነቃ አድኃሪ–የነቃ ሕዝብ

ራሱንም ሆነ ጠቅላላውን ሠርቶ አዳሪ ሕዝብ ነፃ ለማውጣት በሚያደርገው ትግል ወዝአደሩ በተለያየ የንቃተ ሕሊና ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል ። እነዚህን የንቃተ ሕሊና ደረጃዎች ቁርጥ ባለ መልክ ለያይቶ መጠቆም አስቸጋሪ ቢሆንም የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መምህራን ሦስት ዋና ዋና የንቃተ ሕሊና ደረጃዎች ይጠቁማሉ ። የመጀመሪያው ፤ ጨቅላ የሆነው ንቃተ ሕሊና ሲሆን ወዝ አደሩ የሚሰማውን ጭቆና በጠላቱ በቡርዧዋው ላይ ሳይሆን የፋብሪካ መሣሪያዎቹን በመሰባበር ፤ ከመደብ ጓዱ ጋር በኅብረት ሳይሆን በተናጥል እየገነፈለ እንዲታገል የሚቀሰቅሰው ንቃተ ሕሊና ነው ። ነገር ግን በዚህ የጭቆና ውጥረት በሚወልደው ጨቅላ የሆነ ንቃተ ሕሊና ወዝአደሩ ነፃነቱን መጐናጸፍ እንደማይችል በትግሉ ውስጥ እየተደጋገመ የሚደርስበት ውድቀት ያስተምረዋል ።

በሁለተኛው የንቃተ ሕሊና ደረጃ ወዝአደሩ ብቻውን ሳይሆን ከመደብ ጓዶቹ ጋር በኅብረት ፤ በፋብሪካ መሣሪያዎች ላይ ሳይሆን በጠላቱ በቡርዧዋው መደብ ላይ በመነሣት መታገል እንዳለበት ተረድቶ ኑሮውን ለማሻሻል በሞያ ማኅበር ይደራጃል ። በዚህ መልክ የወዝአደሩ መደብ በአንድ በኩል ፤ የቡርዧዋው መደብ ደግሞ በሌላ በኩል ተፋጠው ይታገላሉ። ነገር ግን አሁንም በሞያ ማኅበር ብቻ ተደራጅቶ ለዕለታዊ ጥቅሙ ከቡርዧዋው ጋር በመታገሉ ብቻ የወዝአደሩ መደብ ነፃነቱን አያገኝም ። ዘላቂ ጥቅሙን ለማረጋገጥ ወዝአደሩ የፖለቲካ ሥልጣን ጨብጦ የበላይነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል ። ነገር ግን ወዝ አደሩ ለሥልጣን ብቁ እንዲሆን የግድ ወደ ሦስተኛው የንቃተ ሕሊና ደረጃ መሸጋገር አለበት ። ከዚህ ደረጃ ሳይደርስ በወዝ አደሩ ስም ሌሎች ሥልጣን ይይዙ እንደ ሆነ እንጂ በምንም ዓይነት የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ሊመሠረት አይችልም ።

ሦስተኛው የንቃተ ሕሊና ደረጃ ወዝ አደሩ ዘላቂ ጥቅሙን ለማረጋገጥ በሞያ ማኅበራት መታገል ብቻ እንደማያዋጣው ተገንዝቦ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚታገልበትና ለዚህም ትግል የግድ አስፈላጊ የሆነው የወዝ አደሩ ፓርቲ የሚመሠረትበት ከፍተኛ የንቃተ ሕሊና ደረጃ ነው ። ይህንን ሀቅ ተገንዝበው የሶሻሊዝምን ቲዎሪ ያዋሀዱና የተቀበሉ ምሁራን ተደራጅተው ካላስተማሩትና ካላደራጁት ወዝ አደሩ ከአንደኛው ወደ ሁለተኛው የንቃተ ሕሊና ደረጃ በገዛ ትግሉ እንደተሸጋገረ ሁሉ ከሁለተኛው ወደሦስተኛው ደረጃ በገዛ ትግሉ ብቻ ሊሸጋገር አይችልም ።

በዚህ ጉዳይ ላይ በአድር ባይ ምሁራንና በአብዮታዊ ምሁራን መካከል በሶሻሊዝም ታሪክ ውስጥ እየተደጋገመ የታየ መሠረታዊ ልዩነት አለ ። አድርባይና እወደድባይ ምሁራን ከዚያም አልፎ ጠቅላላው የንዑስ ከበርቴ «ሶሻሊስቶች» ገና በሞያ ማኅበራት በመደራጀትና በመጠናከር ላይ ያለውን ወዝ አደር « ነቅተሐል በቅተሐል» በማለት ወደሦስተኛውና ወደከፍተኛው ደረጃ እንዳይሸጋገር አፍነው ለመያዝ ይሞክራሉ ። ይህ የወዝ አደሩን ንቃተ ሕሊና ማወደስ በእወደድ ባይነት ብቻ የተገፋፋ ፈሊጥ አይደለም ። የቡርዧዋውና የንዑስ ከበርቴው የመደብ ጥቅም የሚጠይቀው ፀረ—ወዝ አደር ታክቲክ ነው ። ለምን ? ምክንያቱም ባለፈው ቁጥራችን በግልጽ እንዳሳየነው ወዝአደሩ የሞያ ንቅናቄውን ከሶሻሊስት ርእዮተ ዓለም ጋር አዋህዶ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚታገልበት የራሱ ፓርቲ እስከሌለው ድረስ በቡርዧዋው መደብ ርእዮተ ዓለም ጥላ ስር እንደወደቀ ይቀራል ። እርግጥ በሞያ ማኅበሩ ወዝ አደሩ ትግሉን መቀጠል ይችላል ። ነገር ግን የፖለቲካ ሥልጣን በቡርዧዋው መደብ እጅ እስከሆነ ድረስ የወዝአደሩ ትግል ሲያይል ቡርዧው በቀኝ እጁ የሰጠውን ትግሉ ሲቀዘቅዝ ደግሞ መልሶ በግራ እጁ ይወስደዋል ። ስለሆነም ከዚህ ወዝ አደሩ ከከበርቴው ጋር እየተደራደረ ጊዜያዊ ጥቅሙን ከማያስከብርበት ደረጃ ከበርቴውን ደምስሶ የፖለቲካ ሥልጣን ጨብጦ ዘላቂ ጥቅሙን ወደሚያረጋግጥበት ደረጃ እንዳይደርስ ፀረ—ወዝአደር ኃይሎች እንዲፍጨረጨሩ የመደብ ጥቅማቸው ያስገድዳቸዋል ። ሦስተኛውን የንቃተ ሕሊና ደረጃ ከጦር ይፈሩታል ። ስለዚህ ወዝ አደሩ በቡርዧው መደብ ርእዮተ ዓለም ጥላ ስር ተወስኖ እንዲቀር ሁለተኛውን የንቃተ ሕሊና ደረጃ እንደ ነሱ የሚያወድስ ፤ የሚያሞግስ ፤ ዕጹብ ድንቅ እያለ የሚያሞካሽ ማንም የለም ።

ወዝአደሩ በዚህ እስከተደለለ ድረስ እውነትም ቡርዧዋውና ንዑስ ከበርቴው ምንም የሚፈሩት ነገር አይኖርም ። ነገር ግን ወዝ አደሩ የሶሻሊዝምን ርእዮተ ዓለም እንዳያዋህድ የሚደረግበትን ማወናበድ ለዘለዓለም አይቀበልም ። የታሪክ ሒደት ወደሦስተኛውና ወደከፍተኛው የንቃት ደረጃ የሚያሸጋግሩበትን ቆራጥና አብዮታዊ ምሁራን ከጐኑ ያሰልፍለታል ። እነዚህ አብዮታዊ ምሁራን ያለአንዳች ማወላወል ያለአንዳች እወደድ ባይነት የወዝ አደሩን ንቃተ ሕሊና ማሞገስ ሳይሆን ያለበትን ደረጃ ጠቁመው ወደከፍተኛው ደረጃ መድረስ እንዳለበት ይነግሩታል ። በዚህ ትግል ኃላፊነት እንዳለባቸው ፤ ይህን ርእዮተ ዓለም ወዝ አደሩ ከገዛ ትግሉ እንደሚያፈልቀው ፤ የግድ ከምሁራኑ ብቻ ሊመጣለት እንደሚገባ አፍረጥርጠው ይናገራሉ ። የነቁት አድኃሪዎች ወዝአደሩን «ነቅተሐል በቅተሐል » እያሉ ሲያወናብዱት እነዚህኛው ደግሞ ንቃ ተደራጅ እያሉ ሳይታክቱ ይወተውቱታል ።

ስለሆነም ንቃት በሚግልበት ጊዜ አንድ መጠንቀቅ ያለብን ነገር አለ።በመሠረቱ ለጥቅሙ የሚተኛ መደብ የለም ። በአድኃሪዎችም በኩል የተለያየ የንቃት ደረጃ አለ ።

ከማቱሳላ ያረጀና ያፈጀ ዜማ ይዞ ከታሪክ ርምጃ ጋር ፤ ከታጋይ ሕዝብ ጋር ፊት ለፊት የሚገጭ አድኃሪ አለ ። ነገር ግን ትግሉ እየገፋ ሲሔድ የአድኃሪውም ታክቲክ እንደዚሁ እየረቀቀ ሊሔድ ይችላል ። የሰፊው ሕዝብ የንቃት ደረጃ ከፍ ማለት አድኃሪዎችን ታክቲክ እንዲቀይሩ ያስገድዳቸዋል ። ያን ጊዜ ነው የነቁ አድኃሪዎች የሚፈለፈሉት ። ያን ጊዜ ነው «ከተራማጅም ተራማጅ ፤ ከኮሚኒስትም ኮሚኒስት ሆነው» ከሰልፉ የሚደባለቁት ።

በፀረ— አብዮት ሴራ እየተራቀቁ የሔዱት ኢምፔሪያሊስቶች የነቁ አድኃሪዎችንና ሠርጎገቦችን ለመመልመል ብዙ ጥረት እንደሚያደርጉ የዓለም ወዝአደሮችን የትግል ታሪክ የተከታተለ ሁሉ ያውቀዋል ። ሠርጎ ገቦቻቸውን በሕዝቡ ትግል ውስጥ ለማስገባት ሌላው ቀርቶ ኢምፔሪያሊስቶች ማርክሲዝምን ለቡችሎቻቸው የሚያስተምሩበት ልዩ ት/ ቤት እስከሚቋቋም እንደደረሱ የታወቀ ነው ። እንዲህ ዓይነቶቹ የነቁ አድኃሪዎች ጨርሰው እስኪጋለጡና በሕዝብ ትግል እስኪተፉ ድረስ ሀቀኛ መስለው ብዙ ሊያወናብዱ ይችላሉ ። በዓለም ወዝአደር ፓርቲዎች የትግል ታሪክ ተደጋግመው የታዩትን የነዚህን የነቁ አድኃሪዎች ታክቲክ ባለፈው ቍጥራችን አመልክተን ነበር ።

በሀገራችን በመካሔድ ላይ ባለው አብዮት የነዚህ ሠርጎ ገቦችና የነቁ አድኅሪዎች ታክቲክ
ጨርሶ ዓይን እያወጣ ሔዷል ። የኤኮኖሚው አሻጥር በግልጽ ነው ። ወዝአደሩ ተወያይቶ እንዳይነቃ
የሚደረግበት ፀረ—ሶሻሊስት መፍጨርጨር ፤ ተደራጅቶ እንዳይታገል የሚሠነዘርበት ፀረ—ድር
ጅትና አናርኪስት ሴራ ፤ የተደራጀውን የወዝ አደር ትግል አቅጣጫ ለማሳየት በየጊዜው የሚሰነዘሩ
በት ትጥቅ አስፈችና አሳሳች መፈክሮች ሁሉ ፤ የነቁ አድኅሪዎችና ፀረ—ሶሻሊስት ኃይሎች የሕዝቡን
ትግል ለመግታት የሚያፍተለትኳቸው ታክቲኮች ናቸው ።

ነገር ግን ማንም ቢሆን ልብ ሊለው የሚገባው ነገር አለ ። አድኅሪዎች እንዲህ መልክና
ገጽታ እየለዋወጡ ለመምጣት የተገደዱት የሕዝብ ትግል እያየለ በመሔዱ ነው ። ስለሆነም በትግሉ
እየገፋ ሲሔድ ታጋዩ ሕዝብ ፊት ለፊት የሚገጥሙትን ጠላቶች ብቻ ሳይሆን መስለው የሚደባለቁ
ትን የነቁ አድኅሪዎችንም መለየት ይጀምራል ። ባለፈው ሰሞን በተደረገው የወዝአደሮች ጉባኤ ሠርጎ
ገቦችን ለማጋለጥ የነቁ ወዝአደሮች ያካሔዱት ኃይለኛ ትግል የነቁ አድኅሪዎች በየረድፉ የሚጋለጡ
በት ዘመን እንደጠባ አብስሯል ።

ይህንን አዲስ የትግል ምዕራፍ በሚገባ ሲተነትን ባለፈው ሰሞን ከጊዜያዊ ወታደራዊ
መንግሥት የተሰጠ መግለጫ የነቁ አድኅሪዎች እንደተነቃባቸው ሲያስረዳ እንደሚከተለው ጽፏል ።

«የኢትዮጵያ ወዝአደሮች አብዮታዊ ንቃታቸው እንዳይዳብርና የተጠነሰሰባቸው ሴራ እየተ
ጋለጠ ሔዷል ፤ ድርጅታቸው እንዳይሰምር የሚሰነዘርባቸው ተንኮል እየከሸፈ ሔድዋል ። ወዳጅ እየመ
ሰለ በመሐከላቸው ውዥንብርንና ሥርዓተ አልባነት አንግሦ ትግላቸውን ለመበተን የሚመክርባቸው
የከሀዲ አናርኪስቶች ማወናበድ ከእንግዲህ ተቀባይነት አይኖረውም ። ይህ ሁሉ ሴራ ፤ ይህ ሁሉ
ተንኮል ፤ ይህ ሁሉ ማወናበድ በነቃና በተደራጀ የወዝአደር ክንድ በመሰባበር ላይ ነው ። ካሁን ወዲያ
የኢትዮጵያ ወዝአደር አድኃሪ ኃይሎችና ጠላቶች አንዱ ፊት ለፊት አንዱ በስተጀርባ ፤ አንዱ በግልጽ
አንዱ በስውር ፤ አንዱ በለየለት ጠላትነት ፤ አንዱ ወዳጅ በመምሰል እየመጡ በትግል የተጎናጸፋቸ
ውን ድሎች ሊነጥቁት እንደሚፈታተኑት ስለሚያውቅ በየትኛውም ገጽታ ፤ ከየትኛውም አቅ
ጣጫ በመጡበት ለመመከት ዝግጁ መሆኑን በማንም ዘንድ መታወቅ ያለበት ሀቅ ነው»
ብሏል ።

የነቁ አድኅሪዎች ግን ይህንን ስለተገነዘቡ ብቻ ትጥቃቸውን አይፈቱም ። ስልታቸው ይበልጥ
የረቀቀ ይሆናል ። ሠርጎ ገብነታቸው ዓይን ከማውጣት ይቆጠባል ። አሻጥራቸው ስውር ይላል ። መፍ
ጨርጨራቸው ግን አያቆምም ። ግን አያሸንፉም ። የኢትዮጵያ ጭቁኖች ታሪካዊ ተጋድሎ ወደ
ፊት እየገፋ በሔደ ቍጥር ለአንድ የነቃ አድኅሪ በሺህ የሚቆጠሩ ታጋዮች ያሰልፍበታልና

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።

« አብዮታዊት ኢትዮጵያ »